# ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፕረስ 6/24/2020፤ የበጋ ትምህርት እና ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመክፈት እቅድ ዝግጅት

**67ኛ ቀን - የበጋ ትምህርት**

በዚህ ሳምንት የተለመደው የበጋ እረፈት ጊዜ ይጀመራል። ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች፣ ሰራተኞችና ወላጆች የበጋ ስሜት ውስጥ የሚገቡበት ወቅት ነው። ነገሮችን ቀዝቀዝ የሚያደርጉበት እና እረፍት የሚወስዱበት ወይም ለጥቂት ቀናት ወደ ሌላ አካባቢ የሚሄዱበት ወቅት ነው።

ለእኛ ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የመጀመሪያው ሳምንት የበጋ እረፍት ጊዜ ከዚህ ትንሽ ለየት ያለ ነው። የእኛን ዝግጅት እና ትምህርት ቤቶቻችን በፎል ወቅት መልሶ ለመክፈት የምናደርገውን ዝግጅት በአዲስ መልክ ለመመልከት እንደ አንድ አጋጣሚ በመጠቀም ላይ ነን። የእኛ ጥረት የሚያተኩሩት በሁለት ቁልፍ መስኮች ነው፤ የትምህርት መርሳት ሁኔታን መቀነስ ስለሆነም የእኛ ተማሪዎች በፎል ወቅት ትምህርት በሚጀምሩት ወቅት ግራ መጋባት ውስጥ እንዳይገቡ ማገዝ እንዲሁም ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመክፈት ዝግጅት ማድረግ- እነዚህ ትልቅ ስራዎች ናቸው እና እነርሱም ሁላችንም እስከ ኦገስት ድረስ እርግጠኛ መሆን በማንችልበት ሁኔታ ውስጥ እንድንቆይ ያስገድደናል። በዚያ ወቅት ሁሉም ተማሪዎቻችን ውጤታማ ለመሆን የሚያስችላቸውን የማህበራዊ ፣ የስሜት እና የአካዳሚ ትምህርት ድጋፍ የሚያገኙበትን የትኛውን የትምህርት አሰጣጥ ሞዴል ወይም ሞዴሎች እንደምንከተል የተሻለ ግንዛቤ ይኖረናል። በዚህ የትምህርት ዓመት የትምህርት አጀማመር ሂደቱ በእርግጠኝነት የተለየ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም። እናም ለእነዚህ ለውጦች አስቀድመን መዘጋጀት ይኖርብናል።

የዛሬው እትም የሚያተኩረው በእነዚህ ሁለት ወሳኝ የበጋ ስራዎች ላይ ነው። ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፕረስ በበጋ ወቅት መዘጋጀት ይቀጥላል። ሆኖም ግን ከአሁን ወዲያ የሚኖረን እትም በሳምንት አንድ ቀን ብቻ ይሆናል። በየሳምንቱ እሮብ ጥዋት ዜናዎችን፣ ማስታወቂያዎችን እና ከቦርድ ስብሰባዎች የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ፣ ስለበጋ ትምህርት መረጃዎችን ፣ እና ትምህርት ቤቶች ስለመክፈት የእቅድ ዝግጅት ሂደት የሚመለከቱ መረጃዎችን እናወጣለን። እባክዎን የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፕረስ በኢሜል መልእክት መቀበያው ላይ ይጠባበቁ። ምክንያቱም በዚህ ላይ ነው ስለትምህርት ቤቶች መልሶ መከፈት እቅድ መረጃ የምናስተላልፈው እና ስለዝግጅቱ አስተያየት ከእርስዎ ለማግኘት የምንችለው ስለሆነም በስራ ላይ እንዲውል የምናደርጋቸው እቅዶች ለተማሪዎቻችን፣ ለቤተሰቦች ሰራተኞች እና የኮሚዮኒቲ አጋሮች የሚያገለግሉ መሆኑን የምናረጋግጠው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከበጋ ትምህርት በፊት ጥቂት ጊዜ እረፍት አድርግ የሚጀመረው ጁላይ 6 ነው። ራስዎን ይጠብቁ፣ ጤናማ ሁነው ይቆዩ - እና በበጋ ወቅት ለእርስዎ ወቅታዊ መረጃ እንደምናቀርብ ቃል እንገባለን!

ከምስጋና ጋር፣

ዶ/ር ግሪጉሪ ሲ .ሐትዚንግስ(Gregory C. Hutchings) Jr. የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንቴንደንት

## የበጋ ትምህርት የሚጀመርበትን ቀን በካላንደርዎ ማስታወሻ ይያዙ

በዚህ ባልተለመደ ወቅት ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ለእያንዳንዱ ተማሪ የትምህርት እድል ለማስፋት ወይም ወጤት ለማሻሻል የሚያግዝ የተሳትፎ እና የማጠናከሪያ ፕሮግራም የያዘ የበጋ ትምህርት እንዲከታተሉ እድል ይሰጣል።

በኮሮና COVID-19 ምክንያት የትምህርት መርሳት ችግር በእርግጥ የሚታይ ችግር ነው። NWEA የተማሪዎችን ለውጥ መመዘኛ በማዘጋጀት እና በመስጠት የሚሰራ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት እንደገመተው ተማሪዎች በፎል ወቅት ወደ ትምህርት (በአካል ወይም በኦንላይን) በሚመለሱበት ጊዜ በሌላ በተለመደው የትምህርት ዓመት ጊዜ ከሚታየው የንባብ ችሎታ አንፃር ሲወዳደር በንባብ በግምት 70% የሚሆን የትምህርት ግብዛቤ ብቻ እንደሚኖራቸው ተገምቶል። በሂሳብ ትምህርት ተማሪዎች በጣም አነስተኛ የሆነ እውቀት እንደሚኖራቸው የተገመተ ሲሆን ከ50% በታች የተማሩትን የሚያስታውሱ መሆኑ ተገምቶል። በሌላ ጊዜ ከሚታየው አንፃር ለአንድ ዓመት ያህል የሚሆን ትምህርት ወደኋላ እንደሚቀሩ ተገምቶል።

ይህን የትምህርት መርሳት ችግር ለመቆቆም ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የበጋ እድሎች የሚያካትቱት የሲክንሮኒክስ እና የአሲንክሮኒክስ የመማሪያ ዘዴዎችን፣ የመማሪያ ጥራዞች እና የአርት ጥበብ ማሳደጊያዎች የትምህርት እድል አዘጋጅቶል። የትምህርት ፕሮግራም አወጣጥ የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች፣የእንግሊዘኛ ቋንቋ (EL) ተማሪዎች፣ ልዩ ስጦታ እና ችሎታ ላላቸው ተማሪዎችን ያካትታል።

**የበጋ ትምህርት የሚሰጠው ከሰኞ እስከ ሐሙስ፣ ጁላይ 6፣ 2020 - ጁላይ 31፣ 2020 ይሆናል።** ሁሉም ተማሪዎች በበጋ ትምህርት እንዲሳተፉ እናበረታታለን። ብዙዎቹ የበጋ ትምህርት ፕሮግራሞች በነፃ ለሁሉም የሚሰጡ ናቸው። ተጨማሪ መረጃዎችን እዚህ ይመልከቱ፤ [ACPS-at-Home website](#).

ለተጨማሪ መረጃ ይህን ይመልከቱ፤ [“Summer Learning for All, Explained!” video](#)




## ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመክፈት የእቅድ ዝግጅት

ከጥቂት ሳምንታት በፊት የቨርጂኒያ ትምህርት ዲፓርትሜንት ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመክፈት መመሪያዎችን አውጥቶል። በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ያሉ ቡድኖችም ይህን መመሪያ ሲያጠኑ እና ይህ መመሪያ ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በፎል ወቅት ምን ተፅእኖ አለው የሚለውን ጉዳይ ሲመለከቱ ቆይተዋል።

ሰሜን ቨርጅኒያ ከሌላው የስቴቱ ክፍል ለየት ባለ አካሄድ መልሶ መክፈት ሂደት ላይ ይገኛል ። እናም የትምህርት ቤቶች ከሴፕቴምበር ባሻግር ዝግ እንደሆኑ የሚቆዩ ከሆነ የድንገተኛ ሁኔታዎችን ያገናዘበ እቅድ ማዘጋጀት ይኖርብናል። ሶስት ሊከሰቱ የሚችሉ ሞዴሎችን መመልከት ይኖርብናል፤ የተለመደው የትምህርት ቤት መከፈት በእርግጥ ይህ ሊኖር የሚችል አይመስልም። ከተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና ቤተሰቦች በሚገኝ መረጃ መሰረት መሻሻል በማድረግ በቨርችዋል የርቀት ትምህርት ሞደል መቀጠል ፤ እንዲሁም የሁለት ሞዴሎች ድብልቅ የማህበራዊ ስብሰብና የማህበራዊ መራራቅ መመሪያዎችን የሚያሟላ አሰራሮችን መከተል።

ከቨርጂኒያ ትምህርት ዲፖርትሜንት የተሰጠውን መመሪያ ስንመለከት በፎል ወቅት በተለመደው መንገድ  ትምህርት ቤቶች በቀደሞው ዓይነት ለመከፈት የሚቻል አይመስልም።  ይህም ከሁላችንም እንደሁኔታው ተለዋዋጭ የሆነ አሰራር መከተልን ይጠይቃል።  በፎል ወቅት ለተማሪዋቻችን፣ ለቤተሰቦቻችን፣ ለሰራተኞቻችን እና የኮሚዮኒታ አጋሮች የትኛው አማራጭ የተሻለ ምርጫ መሆኑን ከመወሰናችን በፊት እኛ መፍትሔ ማግኘት ያለብን ብዙ ያልታወቁ ነገሮች አሉ።  በዚህ ባልተለመደ ጊዜ እባክዎን ትግስትዎን እንዲያሳዮን እንፈልጋለን።  አዳዲስ መረጃዋች ስናገኝ ለእርስዎ የምናሳወቅ መሆኑን እንገልፃለን።

ስለትምህርት ቤቶች መልሶ መከፈት ጉዳይ ዝርዝር መረጃ እዚህ Update Center tab በሚለው ዌብሳይት ገፅ ስር ማግኘት ይቻላሉ፤ ACPS-at-Home website

ትምህርት ቤቶችን መልሶ መከፈት እቅድን ዝግጅት ሂደት የተለያየ የአሰራር ሂደትን አሉት፤  የሚከተሉትን ያካትታል፤

- መመሪያዋችን ከእኛ የሃሳብ አጋሮች ማሰባሰብ Thought Partners: የከተማው፣ በከተማው ከሚገኙ የኮሚዮኒቲ መሪዋች፣ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሰራተኞች ያቀፉ የመሪዋች ቡድን።
- ዋነኛ በሆኑ ጉዳዮችን አንድ አይነት አሰራር ለመፈጠር በኖርዘርን ቨርጅኒያ ካሉ ከሌሎች የትምህርት ቤቶች አስተዳደር ዲቪዝን ጋር ትብብር ማድረግ ።
- በሃሳብ አጋሮች እና በቨርጂኒያ ትምህርት ዲፖርትሜንት የተሰጡ መመሪያዋችን በመጠቀም አምስት የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ዘርፈ ብዙ ተግባራዊ የሚሆኑ የእቅድ ዝግጅት ቡድኖች   ሶስት ሞዴሎችን እቅድ ማዘጋጀት (ከላይ የተገለፁትን)።  በእያንዳንዱ አምስት ዘርፎች የሚከተሉት ጉዳዮ የሚመለከታቸው አካላት ተሳታፊ ናቸው፤ ተማሪዋች፣ ሰራተኞች፣ ወላጆች እና የኮሚዮኒቲ አጋሮች። ይህ ስራ በመላው የትምህርት ቤት አስተደደር ዲቪዝኑ በቡድን መሪዋች አማካኝነት የቅንጅት ስራ ይካሄዳል።
- የተመረጡ ቡድኖች አስተያየት ይሰባሰባል። የተማሪዋችን ፍላጎት ማካተታችንን እና ሁሉም አሳሳቢ የሆኑ ጉዳዮችን ምላሺ ማግኘተቻውን ለማረጋገጥ ለጥናት የተመረጡ ቡድኖች፣ ርእሰ መምህሮች ፣ ሰራተኞች፣ ተማሪዋች፣ ወላጆች እና የኮሚዮኒቲ አጋሮች የያዘ መሆኑ አስፈላጊ ነው።
- ከሱፐር ኢንቴንደንት ጋር የተያቀ እና መልስ መልኩ ዌብሚናር በመካሄድ  አስተያየት ማሰባሰብ ፣ በፎል ወቅት በስራ የሚውለውን ሞዴል ከመመረጡ በፊት ከሰራተኞች፣ ተማሪዋች ፣ ወላጆች ፣ እና ከኮሚዩኒቲ አጋሮች የሃሳብ ማሰባሰቢያ ቅፅ ማሰባሰብ ።

በቀጣይ ጉዳዮ መከታተል ይፈልጋሉ? ሁሉም ስብሳባዋች የሚቀረፁ ሲሆን በዚህ ACPS-at-Home ድረገፅ ላይ እንዲወጡ ይደረጋል፤  Reopening Schools Planning Timeline

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዋነኛ ቀናትን  በካላንደር ማስታወሻ እንዲይዙ ለእናንተ ማሳወቅ እንፈልጋለን። በዚህ ትምህርት ቤቶች መልሶ መከፈት የእቅድ ዝግጅት ሂደት በየደረጃው እርስዎ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያስችላል።

**ቅዳሜ፣ ጁን 26-**  የእቅድ ዝግጅት ሂደት አጠቃላይ መግለጫ እና ለምርጫ የሚቀርቡ የሚችሉ ሞዴሌች ለትምህርት ቤት ቦርድ እንዲመለከተው ይቀርባል። የትምህርት ቤት ቦርድ ስብስባውን በቀጥታ ሲካሄድ በዚህ ይከታተሉ፤  School Board Meetings webpage.

**እሮብ፣ ጁላይ 1-**  ለትምህርት ቤት ቦርድ በጁን 26 ስባሰባ የቀረበው የእቅድ ዝግጅት ሂደት ማጠቃላያ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፐረስ ይቀርባል።  ይህም የሚያካትተው በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ይህን ትምህርት ቤቶች መልሶ የመከፈት እቅድ ዝግጅት ሂደት በተመለከተ ያደረገውን ውይይት መመልከት ይቻላል።

**ጁላይ 6 - ጁላይ 13** - በፎል ወቅት የሚቀርቡትን አማራጮች  በተመለከተ የጥናት አትኩሮት ቡድን የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሰራተኞች፣ ወላጆች፣ ተማሪዋች እና የኮሚዮኒቲ አጋሮች ስብሰባ ይካሄዳል።

**ጁላይ 6 - ጁላይ 13-**  ዌብሚናር ይካሄዳል እና የትምህርት ቤቶች መልሶ መከፈት በተመለከተ ከህዝብ አስተያየት ይሰበሰባል።

**እርብ፣ ጁላይ 17-** የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ዘርፈ-ብዙ የተግባር እቅድ ዝግጅት ቡድኖች ስራ እንቅስቃሴዎች በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ይቀርባል። የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባውን በቀጥታ ሲካሄድ በዚህ ይከታተሉ፤ School Board Meetings webpage.

**እሮብ፣ ጁላይ 22-** የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ዘርፈ-ብዙ የተግባር እቅድ ዝግጅት ቡድኖች ስራ እንቅስቃሴዎች ማጠቃለያ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፕረስ ይቀርባል። ይህም የሚያካትተው በትምህርት ቤት ቦርድ የጁላይ 17 ስብሰባ ይህን ትምህርት ቤቶች መልሶ የመከፈት እቅድ ዝግጅት ሂደት በተመለከተ የሚደረገውን ውይይት ይመለከታል።

**አርብ፣ ኦገስት 7 -** ይህ ለቨርጂኒያ የትምህርት ዲፖርትሜንት ሪፖርት የሚደረው በፎል ወቅት የሚቀርቡትን አማራጮች በተመለከተ የሚዘጋጀው ረቂቅ እቅድ ለህዝብ እና የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሰራተኞችን፣ ወላጆች፣ ተማሪዎች እና የኮሚዩኒቲ አጋሮችን ላካተተው የጥናት አትኩሮት ቡድን ይገለፃል ። ሊመረጡ የሚችሉ ሞዴሎች እና ሰራዎች ክንውን አጠቃላይ መግለጫና በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ዘረፈ ብዙ ተግባር እቅድ አዘጋጅ ቡድኖች እስከዚያ ድረስ የተከናወኑ ስራዎችን ለትምህርት ቤት ቦርድ ይቀርባል። የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባውን በቀጥታ ሲካሄድ በዚህ ይከታተሉ፤ School Board Meetings webpage.

**እሮብ፣ ኦገስት 12-** በፎል ወቅት ትምህርት ቤቶች መልሶ ለመከፈት የሚዘጋጀው የመጨረሻው እቅድ በኤ.ሲ.ኤ.ኤስ. ኤክስፕረስ ይቀርባል። እቅዱ ለእርስዎና ለልጅዎ ምን ማለት እንደሆነ እርስዎ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች መልክ በተጨማሪ ይቀርባል።

ከዚህ በተጨማሪ ከእነዚህ ቁልፍ ክንውኖች በተጨማሪ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፕረስ ሳምንታዊ ወቅታዊ መረጃዎች ይቀርባሉ።

## ስለ ትምህርት ቤቶች መልሶ መከፈት ለእናንተ ጥያቄዎች መልስ

ባለፈው የጥያቄና መልስ ዝግጅት ሱፐር ኢንቴንደንት ዶ/ር ግሪጎሪ ሲ. ሐትቺንግስ (Gregory C. Hutchings, Jr) ትምህርት ቤቶች መልሶ ለመከፈት የእቅድ ዝግጅት በሚሰሩበት ወቅት የሚያገለግላቸውን የቨርጂኒያ ትምህርት ዲፓርትሜንት (VDOE) መመሪያዎች በተመለከተ ምላሽ ሰጥተዋል። ሙሉውን መረጃ እዚህ ያንብቡ፤ Virginia Department of Education guidance (PDF)

ዶ/ር ሐትቺንግስ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል፤

- **አገረ ገዢው በትምህርት መጀመሪያ ቀን ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤታቸው እንደሚመለሱ ይጠብቃሉ?**
- **ትምህርት ቤቶችን ለመከፈት የስቴቱ መመሪያ እና የስቴቱ እቅድ ምን ይመስላል ?**
- **እኛ የመልሶ መከፈት እቅድ ዝግጅት ሂደት የቨ.ዲ.ኦ.ኢ. ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ የሚያቀርበው ሃሳብ ምክር እንዴት ነው?**
- **የቨ.ዲ.ኦ.ኢ. የትምህርት ቤቶች መቼ መልሶ መከፈት የተመለከተ የሚቀርበው ሃሳብ ምን ይመስላል?**
- **ከቨ.ዲ.ኦ.ኢ. ከቀረበው ሃሳብ ጋር የሚጣጣም ትምህርት ቤቶችን መልሶ የመከፈት አሰራር ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በማዘጋጀት ላይ ነው?**
- **የቨ.ዲ.ኦ.ኢ. የበጋ ትምህርት እንዲካሄድ ሃሳብ ያቀርባል?**

የጥያቄና መልስ ቪዲዮ ይመልከቱ Watch the Q&A video ወይም ለጥያቄዎች የተሰጠውን መልስ በዚህ ላይ ይመልከቱ፤ updated FAQ.

ተጨማሪ መረጃዎች የጥያቄና መልስ ጭምር Reopening Planning በACPS-at-Home ድረገፅ ላይ Update Center በሚለው ገፅ ስር ማግኘት ይቻላል።

## የእኛን ወደጡረታ እረፍት የደረሱትን ማክበር

አንዳንድ የስራ ባልደረቦቻችን ቀጣዩን የህይወት ዘመናቸውን በሚጀምሩበት በዚህ ወቅት የምንሰባትበትና መልካም የምንመኝበት ጊዜ ነው ። የዚህ ዓመት ስነስርዓቱ የሚካሄደው በቨርችዋል በርቀት ነው። Watch now:




## የሁለተኛ የዳሰሳ ጥናት መጠይቅ ውጤት ታውቋል።

በጁን 8 እና ጁን 14 መካከል ባለው ጊዜ የሁለተኛ የዳሰሳ ጥናት መጠይቅ 10,631 ምላሾችን አገኝተናል። 1,684 ከሰራተኞች፣ 3,434 ከተማሪዎች፣እና 5,513 ደግሞ ከወላጆች ነበር የተገኘው። ከወላጆች የተገኘው 1,200 የሚሆነው የመጠይቁ ምላሺ የቀረበው ከእንግሊዘኛ ሌላ ቋንቋ ነበር። በሜይ ወር በመጀመሪያ ከተዘጋጀው መጠይቅ 700 ምላሺ ጭማሬ ታይቶል።

በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በቀረበው በማህበራዊ እና የስሜት ድጋፍ በተመለከተ ከፍተኛ እርካታ እንዳለ ታውቋል። ሆኖም ግን የትምህርት አሰጣጥ፣ የትምህርት ቤት ግንኙነት ፣ የአስተማሪ/የትምህርት ግንኙነት እና የማህበራዊ እና የስሜት ጤንነት ጉዳዮ የሚመለከታቸው አካላት ላይ አትኩሮት መስጠት እንደሚያስፈልግ መረዳት ተችሎል።

**ጥንካሬ የታየባቸው መስኮች**

- ወላጆች (78%)፣ ተማሪዎች (85%) እና ሰራተኞች (80%) በትምህርት እና የአካዳሚ ድጋፍ አሰጣጡ ስራ ከፍተኛ እርካታ እንዳለቸው ገልፀዋል።
- አብዛኛዎቹ ወላጆች (74%) ፣ ተማሪዎች(75%) እና ሰራተኞች (83%) በማህበራዊ እና የስሜት ድጋፍ አሰጣጥ የረኩ መሆናቸውን አሳውቀዋል። ምንም እንኳን ይህ ጉዳይ ባለፈው መጠይቅ ላይ ከተገኘው ውጤት አኳያ ዝቅ እንዳለ ቢያሳይም።
- ሰራተኞች (82%) እና ተማሪዎች (72%) የሚሰማቸው ጭንቀት ሃሳብ በአግባቡ መምራት የቻሉ መሆኑ ታውቋል።

**በቀጣይ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች፤**

ሁለተኛ ዙር ውጤቶች በአብዛኛው ከአንደኛው ዙር ጋር ተመሳሳይ ናቸው። በመጀመሪያው ዙር የተለዮ አትኩሮት የሚፈልጉ ጉዳዮች (በቅድሚያ የተማሪዎች ተሳትፎ) በሁለቱ መጠይቆች #1 እና # 2 መካከል ሲነፃፀር ለውጥ አልታየበትም። እንዲያውም በአነስተኛ መልክም ቢሆን ዝቅ ብሎል።

- አስተማሪዎች በሁለተኛ ዙር የተማሪዎች ተሳትፎ እንደቀነሰ ገልፀዋል 63% የሚሆኑት ሪፓርት ያደረጉት ከግማሽ በታች የሆኑት ተማሪዎች ባላፈው ሳምንት በክፍል ትምህርት ተሳትፎ ያደረጉ መሆናቸውን ገልፀዋል። ( በ1ኛ ዙር 54% ጋር ሲነፃፀር።)

- የመቀራረብ ግንኙነት ስሜት በቤተሰቦችና በአስተማሪዎች መካከል ቀንሶል። (ተማሪዎች ከአስተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸው መቀራረብ ከ74% ወደ 70% ቀንሶል ፣ የወላጆች ከትምህርት ቤት ጋር ያላቸው ግንኙነት 81% ወደ 74% ቀንሶል እና አስተማሪዎች ከተማሪዎች ጋር ያላቸው የመቀራረብ ስሜት 68% ወደ 63% ቀንሶል ።)

የተገኘው ውጤት የበጋ ትምህርት እቅድ (3.0) እና ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመክፈት የእቅድ ዝግጅት(4.0) በስራ ለማዋል እገዛ አድርጎል።

ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ እና ተሳታፊዎች እነርሱን ምቹ የተረጋጋ ስሜት እንዲኖራቸው ለማድረግ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ማተኮር ስለሚኖርበት ጉዳዮች ተሳታፊዎች ያለገደብ የገለፁትን ሃሳቦች ጭምር የሚያሳዩ ውጤቶችን ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመክፈት ለተደራጀው ዘርፈ-ብዙ የእቅድ አዘጋጅ ቡድኖች እንዲያውቁት ይደርጋል። መረጃው በተጨማሪ ሊኖር የሚችል ኢፍትሃዊነትን (inequities) ለማጠራት እና አጎልቶ ለማሳየት አገልግሎት ላይ ይውላል።

ሙሉ ሪፓርቱ እንደተዘጋጀ ወዲያውኑ በዚህ ገፅ ላይ እንዲወጣ ይደረጋል፤ACPS-at-Home

## የአርብ ቀን የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ይከታተሉ።

በአርብ ቀን የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ወቅት የትምህርት ቤት ቦርዱ በJuneteenth ቀን የታየውን የፀረ ዘርኝነት አቆም በማረጋገጥ ስርዓታዊ ዘርኝነት የሚያወግዙ መሆናቸውን እና ለሁሉም ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና ሰራተኞች የትምህርት ፍትሃዊነት እንዲኖር ያላቸውን ቁርጠኝነት ባወጡት የአቆም መግለጫ ላይ በመፈረም አረጋግጠዋል።

የትምህርት ቤት ቦርድ the resolution - በዩናይትድ ስቴት የባርነት ስርዓቱ እንዲቆም የተደረገበት የነፃነት ቀን በሚል የሚታወቀው ቀን የJuneteenth በተመለከተ ያለምንም ተቃውሞ አፅድቆል።

ቦርዱ በተጨማሪ ውይይት ያደረገው፤

- ስለትምህርት ተቆማት የበጋ ፕሮጀክቶች፡
- ስለ 2020--21 የሣሙኤል ተከር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የትምህርት ዓመት ካላንደር መቀየር ።
- አዲስ የማህበራዊ ጥናቶች የመማሪያ መፅሀፍ መወሰን።
- የሁለተኛው የኮሮና COVID-19 ዳሰሳ ጥናት መጠይቅ ውጤቶች ።

በቀጥታ የሚተላለፈውን ካልተከታተሉ እዚህ ላይ መመልከት ይችላሉ፤ የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ይከታተሉ፤ Watch the School Board meeting and see the agenda.

ለትምህርት ቤት ቦርድ እንዴት አስተያየት መስጠት እንደሚችሉ ለማወቅ ከፈለጉ መረጃ እዚህ ማግኘት ይችላሉ፤ School Board Meetings webpage.

## አዲስ ሰዓታት ለጥምር ቋንቋ አገልግሎት የመረጃ መስመሮች

የኤፍ.ኤ.ሲ.ኢ.(FACE) ማእከል የጥምር ቋንቋ ተናጋሪ የወላጆች የመረጃ መስመር አሁን ከሰኞ - አርብ ከጥዋት 9.00 እስከ 1.00 ቀን ድረስ ይኖራል።

- **የስፓኒሽ/እንግሊዘኛ 571-775-9719 ስልክ ይደውሉ።**
- **የአማርኛ/እንግሊዘኛ 703-927-6866 ስልክ ይደውሉ።**

- **የአረብኛ/እንግሊዘኛ 703-927-7095 ስልክ ይደውሉ።**

## ለጁላይ 4 የሳምንቱ መጨረሻ ቀናት የምግብ ክፍፍል ለውጥ ጠቃሚ መረጃ

**በምግብ ማከፋፈያ ቦታዎች እና ተንቀሳቃሽ ቦታዎች ከነፃነት ቀን በዓል አስቀድሞ ባለው አርብ ቀን ጁላይ 3 ቀን የምግብ ስርጭት አይካሄድም።** ሆኖም ግን እሮብ፣ ጁላይ 1 ቀን መጪውን በዓል ጊዜ እንዲሸፍን ተጨማሪ ምግብ እንዲከፋፈል ይደረጋል። የተለመደው የምግብ ክፍፍል አገልግሎት ተመልሶ ሰኞ፣ ጁላይ 6 ቀን ይጀምራል።

**አዲስ!** ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተጨማሪ የምግብ ማከፋፈያ ፕሮግራም አዘጋጅቶል። አርብ በሁሉም የምግብ ማከፋፈያ ቦታዎች እና በተንቀሳቃሽ ቦታዎች የሚካሄደው የምግብ ስርጭት አርብ፣ ቅዳሜ እና አሁን ደግሞ እሁድን እንዲሸፍን ተደርጎል።

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የወቅቱ የምግብ ክፍፍል አሰራር ሞዴል እስከ ኦገስት 21፣ 2020 ድረስ በነበረው ሁኔታ ይቀጥላል።

ስለምግብ አቅርቦት ተጨማሪ መረጃ የምግብ አቅርቦት ገፅን ይመልከቱ፤ ACPS-at-Home website.

---

ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዎችና እድሚያቸው ከሁለት አመት በላይ ለሆኑ ልጆች የምግብ አቅርቦት ብዙ የማከፋፈያ ቦታዎች በአሌክሳንደሪያ ከተማ አሉት።

**ይዞ-መሄድ የምግብ ማከፋፈያ ቦታዎች:**

ይዞ መሄድ ቁርስ፣ ምሣ እና መክሰስ (ስናክ) ምግቦች ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ከጥዋት 8.00 እስከ ከቀኑ 12.00 ድረስ በሚከተሉት ቦታዎች ይሰጣል፤

- **ዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት**
  5700 Sanger Avenue Alexandria, VA 22311
- **የፍራንሲስ ሲ ሐመንድ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**
  4646 Seminary Road, Alexandria, VA 22304
- **ኮራ ኬሊ አንደኛ ደረጃ የሂሳብ፣ ሳይንስ እና ቴክኒዋሎጂ ት/ቤት፤**
  3600 Commonwealth Avenue, Alexandria, VA 22305
- ጀፈርሰን ሁዊስተን ቅደመ-መደበኛ - 8ኛ IB ትምህርት ቤት
  1501 Cameron Street, Alexandria, VA 22314
- **የቲ.ሲ. ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**
  3330 King Street Alexandria, VA 22304

እንዲሁም "ተንቀሳቃሽ - ፓፕ አፕ" የማከፋፈያ ቦታዎች የሚገኙበት ቦታዎች፤

- **ሜሶን አፓርትሜንት(Mason Apartments)** በ South Reynolds Street Alexandria, VA 22304
  ከ10:45 - 11:15 ጥዋት ሰኞ ፣ እሮብ እና አርብ

- **ብረንት ፕሌስ አፓርትሜንት (Brent Place Apartments) በ 375 South Reynolds Street, Alexandria, VA 22304** 11:20- 11:50 ጥዋት ሰኞ ፣ እሮብ እና አርብ

- **ሩቢ ተከር የቤተሰብ ማእከል (Ruby Tucker Family Center) በ 322 Tancil Court, Alexandria**, VA 22314 10:45 - 11:15 **ጥዋት ሰኞ ፣ እሮብ እና አርብ**

- **ኮሚዮኒቲ ሎጂንግ (Community Lodgings) በ 607 Notabene Drive, Alexandria, VA 22305** ጥዋት 10:45 - 11:15 ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ።

- አልድ ታወኒ ዌስት (**Old Towne West) አፓርትሜትን (የመኪና ማቆሚያ) በ 500 South Alfred Street, , Alexandria, VA 22314**
ጥዋት 11:20 - 11:50 ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ።

- ***ፎሎረንስ ድራይቭ እና ፎር ማይል መገናኛ መንገድ*(Florence Drive እና Four Mile Road) Alexandria, VA 22305** ከጥዋት 10:45 - 11:15 ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ቀናት።

- ***ዘ ፊልድስ* (The Fields) በ 4309 Duke Street, Alexandria, VA 22304** ጥዋት 10:45 - 11:15 ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ።

- ***በቤንጊተን ክሮኒሲንግ* (Bennington Crossing) አፓርትሜንት በ 441 North Armistead Street, Alexandria, VA 22312** ጥዋት 11:30 እስከ እኩለቀን ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ቀናት ።

**ምግብ ለማግኘት ምዝገባም ሆነ ስም መፃፍ አያስፈልግም።**

ምግብ የያዘው ቁርስ፣ ምሣ እና መክሰስ (ስናክ) እንዲሁም ለምሳሌ ትኩስ ፍራፍሬ እና አታክልት እና ለብዙ ቀናት የሚሆን ሳንዱች።

**<u>ማስታወሻ፤</u> ማክሰኞ እና ሐሙስ ምንም የምግብ ክፍፍል አይኖርም።** የተወሰኑ ቀናት እንዲሆን መደረጉ የሶሻል መራራቅን አሰራር ለመከተል እና አስፈላጊ ያልሆኑ ግንኙነቶችን ለመቀነስ ነው። ለሁለት ቀናት የሚሆን ምግብ ሰኞ እና እሮብ ቀናት ይከፋፈላል እንዲሁም አርብ ለሶስት ቀናት የሚሆን ምግብ ይሰጣል።

**የአሌክሳንደሪያ ከተማ ሌሎች የምግብ አቅርቦት ምንጮች**

በአሌክሳንደሪያ ከተማ የምግብ ማቅረቢያ በታዋች እና ሰዓት የጊዜ ሰሌዳ ለማወቅ ይህን ይመልከቱ። www.hungerfreealexandria.com ወይም ስልክ 703-662-1067. .

**ጥያቄዋች? ወይም አስተርጎሚ ይፈልጋሉ?**

ጥያቄዎን በስፓኒሽ፣ በአረብኛ ወይም በአማርኛ ቴክስት ያድርጉ፤
- ACPSMEALS to 797979 (እንግሊዘኛ እና ስፖኒሽ፤)
- ለ703-927-6866 ይደውሉ ወይም ቴክስት ያድርጉ (በአማርኛ )
- ለ703-927-7095 ይደውሉ ወይም ቴክስት ያድርጉ (በአረብኛ )

ወይም

የኤፍ.ኤ.ሲ.ኢ.(FACE) ማእከል የጥምር ቋንቋ ተናጋሪ የወላጆች የመረጃ መስመር አሁን ከሰኞ - አርብ ከጥዋት 9.00 እስከ 1.00 ቀን ድረስ ይኖራል።
- የስፓኒሽ/እንግሊዘኛ 571-775-9719 ስልክ ይደውሉ።

- የአማርኛ/እንግሊዘኛ 703-927-6866 ስልክ ይደውሉ።
- የአረብኛ/እንግሊዘኛ 703-927-7095 ስልክ ይደውሉ።

**የደህነት ማስታወሻ**

እባክዎን ያሳታውሱ በእርስዎ እና በሚቀጥለው ቤተሰብ ወይም ሰዎች መካከል በምግብ ማከፋፈያ ቦታዎች ስድስት ፊት ርቀት በመጠበቅ የሶሻል ዲስታንሲንግ (ተራርቆ መቆም) አሰራር ያክብሩ።

ማንኛውም የመተንፈሻ አካላት ህመም ምልክቶች ያሉት ሰው ለምሳሌ ትኩሳት፣ አፍንጫ መዝረክረክ፣ የሚከረከር ጎሮሮ ፣ ሳል፣ ወይም የመተንፈስ ችግር የምግብ ክፍፍል በሚደረግበት ቀን ወይም ከዚያ ቀን 24 ሰዓት በፊት ከለብዋት እባካችሁ ወደ ምግብ ማከፋፈያ ቦታ አይምጡ። እና ወደ ጤና አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ይደውሉ። የራስዎ ሐኪም ከሌለዋት እና በክሊኒክ ያልተመዘገቡ ከሆነ የአስቸኳይ ጊዜ ህክምና ወይም የድንገተኛ ጊዜ ህክምና ቦታ ይደውሉ።

## የወጣቶች ጤንነት ማእከል አሁንም ክፍት ይሆን

የወጣቶች ጤንነት ማእከል በቲ.ሲ. ዊሊያም አሁንም በተለመደው የስራ ሰዓት ክፍት ነው ከሰኞ እስከ አርብ ለሁሉም የአሌክሳደንሪያ ወጣቶች ከ12-19 ለሆኑት። በክሊኒክ ሁሉም አገልግሎቶች ይሰጣሉ እና አንድ ወጣት ትኩሳቱ/ቶ (100.0 ወይም ከዚያ በላይ) ከሆነ በስልክ ጤና ቪዲዮ ከእነሱ ጋር መገናኘት እንችላለን። በስልክ በመደወል ቀጠሮ መያዝ ይቻላል 703-746-4776።

## ከአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት ወቅታዊ መረጃ

የስቴቱን በቤት ቆዮ ትእዛዝ ሁሉም ሰው እንዲያከብር የአሌክሳንደሪያ ከተማ እና የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት አጥብቆ ይመክራል በጣም አስፋላጊ የሆኑ የምግብ ግዢ እና የህክምና ጉዳይ ለመውጣት ካልሆነ በስተቀር እንዲሁም ህዝብ በሚኖርበት ቦታ 6 ፊት (1.80 ሜትር) ርቀት መጠበቅን እንዲያከብሩ ይመክራል። የኮሮና ባይረስ COVID-19 እንዳይስፋፋ በማድረግ የእርስዎ ጎረቤት እና ቤተሰቦች በእርስዎ ላይ ነው እምነት የጣሉት። ስለቫይረሱ COVID-19 ለተጨማሪ ጥያቄዋች ስልክ 703.746.4988, በስራ ሰዓታት ከጥዋት 9፤00 እስከ 6 ከሰዓት በኋላ ይደውሉ፤.

ተጨማሪ መረጃዋች በዚህ ይገኛል፡ www.alexandriava.gov/Coronavirus.




## የCOVID-19 ፍርሃትና አለማወቅን መቆቆም

የአሌክሳንደሪያ ከተማን ድረገፅ ጎብኝ ፤ Coping with COVID-19 Fear and Uncertainty ይህን ይጨምራል COVID-19 Wellness Resource Guide.

## መርዳት ይፈልጋሉ?

እባክዎን የሚችሉ ከሆነ ለ**ACT For Alexandria** ድጋፍ ያድርጉ እና **Covid-19 Response Fund** ።

የኮሚዮኒቲ አባል በበጎ ፈቃደኝነት ማገልገል የሚፈልግ በዚህ ሊመዘገብ ይችላል www.volunteeralexandria.org ወይም 703-836-2176 ሌሎች የበጎ ፍቃደኝነት አገልግሎት ለመስጠት።

## የአእምሮ ጤና ድጋፍ

**የትምህርት ቤት ድጋፍ ሰጪ አገግሎት ቀጣይነት እና የአካዳሚ ምክር**

የትምህርት ቤቱ ሶሻል ሰራተኛ፣ የትምህርት ቤቱ ነርስ፤ የትምህርት ቤት አማካሪ፣ የት/ቤት ሳይኮሎጅስት ፣ የተማሪ ድጋፍ ቡድኖች በዚህ ዝግ ወቅት በስራ ላይ ይሆናሉ ከሰኞ እስከ አርብ ከጥዋት 8.30 እስከ 3.30 ከሰዓት በኋላ ድረስ ሰራተኞች ከተማሪዎች እና ከቤተሰቦች ጋር ይገናኛሉ። የተማሪዎች አገልግሎት የአማራጭ ፕሮግራም እና ፍትሃዊነት ዲፓርትሜንት ሰራተኞች በዚህ ግዜ በስራ ላይ ይሆናሉ እና በስልክ እና በኢሜል ይገኛሉ፤ student_services@acps.k12.va.us ።

**የድንገተኛ ሁኔታ ድጋፎች**

የድንገተኛ ሁኔታ ሲፈጠር በዚህ የዝግ ወቅት ተማሪዋችና ቤተሰቦች የሚከተሉትን ድጋፎች ማግኘት ይችላሉ፡

- Crisis Text and Crisis Link:
    - ቴክስት CONNECT to 85511
    - .ስልክ፤ 703 -527-4077
- Alexandria Safe Place
- የአሌክሳንዳሪያ የ24 ሰዓት የአእምሮ ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት Alexandria City 24-Hour Emergency Mental Health Services
- የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርትሜንት Alexandria City Health Department and AHD Contacts
- Inova Alexandria Hospital (ER)

ፈታኝ ጊዜ እንደሆነ እናውቃለን። በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ድረገፅ፤በማህበራዊ ሚዲያ እና በኢሜል መረጃ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ያሰራጫል። ማንኛውም ጥያቄ ሲኖር ከትምህርት ቤቱ ሶሻል ሰራተኛ እና አማካሪ ጋር ከመገናኘት ወደኋላ አይበሉ።

## የጤና ጉዳይ ማሳሰቢያዋች

**ጤንነት አይሰማዎትም?**

ከቤተሰብ ሀኪም ጋር ይገናኙ፤ ምንም የጤና ኢንሹራንስ የለዎትም? ከኔበርሁድ ሄልዝ(Neighborhood Health) ጋር በስልክ ይገናኙ 703-535-5568.

---

**ጥያቄዋች፣ አሳሳቢ ጉዳይ ወይም አስተያየት ? ከእኛ ጋር ይገናኙ፤.**

***ጤናማ ሁነው ቆዩ!***

***እጅዎን ሁልግዜም ይታጠቡ፡፡ የተለመደው ሳሙና በቂ ነው፡፡***